# የአቶ፡ኸርማን፡ኮኸን፡እና፡የኢትዮጵያ፡ችግር።

ገጽ፡፩-፪፤ የካቲት፡፪፡ቀን፡፪ሺ፬፡ዓመተ፡ምሕረት።




ከሁሉሉ፡አስቀድመን፡የኢሳትን፡አባላት፡በሙሉ፡በአቶ፡አበበ፡ገላው፡አማካኝነት፡ከልብብ፡እናማሠግናለን።አቶ፡አበበ፡ገላውንም፡በሙያተኛ፡አጥጠያዪቃቸው፡እጅግ፡በጣም፡እናመሠግናለን።ሁለትኛም፡የቀዳማዊ፡ኃይለ፡ሥላሴ፡ዘመነ፡መንግሥት፡እንደራሴ፡እና፡ስማቸው፡እንዳይገልለጽ፡ያሳሰቡንን፡ስለ፡አቶ፡ኸርማን፡ኮኸን፡ጥያቄ፡አምመላለስ፡ለጠዬቅናቸው፡ተባባሪነት፡እንዲሁ፡ከልብብ፡እናመሠግናልለን።

ከሚያሳዝነን፡ደግሞ፡እንደ፡ኢትዮጵያ፡ላልለች፡ሉዓላዊት፡አገር፡ኸርማን፡ኮኸንን፡የመስሰለ፡የውጭ፡ዜጋ፡ሦስት፡ተገንጣይ፡ቡድኖችን፡በማናቸውም፡ሁኔታ፡እያገዘ፡አገር፡ካስወረረ፡በኋላ፡አሁንም፡ያለመፀፀቱ፡ጉዳይ፡ነው።የአመሪካ፡መንግሥታቸው፡ስለላ፡ከፍል፡ባስጠናቸው፡ተገንጣዮችን፡ብቻ፡ለይቶ፡መግለጫቸውን፡እራሳቸው፡እያነበቡ፡እና፡ለይስሙላ፡“ዴሞክራሲ፡ከሌለ፡ትብብር፡የልለም”፡በማለት፡በብዙኀን፡መገናኛው፡ከማስሰማት፡ሌሎች፡ኢትትዮጵያውያን፡ምሁራንን፡ቀርበው፡አለማነጋገራቸው፡ስውር፡ሤራ፡ነው።“ሐሣባችን፡ወያኔ፡አዲስ፡አበባን፡እንዲቆጣጠር፡እንጂ፡እንደዚያ፡እንዲይዝ፡አልነበረም”።ያሉትን፡ባለሙያተኛ፡ምሁራን፡ምን፡ትርጉም፡ሰጥተውት፡ይሆን።ይኸን፡ካልን፡በኋላ፡ድምፃዊው፡ባለሙያ፡ዘማሪ፡ፋሢል፡ደመወዝ፡እንዳለው፡-



“..........አርረሱት፡ይሉኛል፤አርረሱት፡.........ይሉኛል፡የሑመራን፡መሬት፤የመተማን፡መሬት፤የአርማጭሆን፡መሬት፤ያውም፡የኛን፡ዕጣ፤ እነሱ፡ምን፡ያርጉ፡ከኛ፡ሰው፡ሲትታጣ”። በመሆኑ፡ማንም፡እዬተነሣ፡በአገራችን፡ሲፈነጭብባት፡ምሁራን፡ልጆቿ፡አንተ፡ማነህና፡አለማለታቸው፡ትንግርት፡ነው።

**Fasil Demoz**

www.youtube.com

“ኤርትራ፡ከኢትዮጵያ፡እንድትገነጠል፡አላደረግንም፡እያሉ፡የቀድሞው፡ባለ፡ሥልጣን፡ኸርማን፡ኮኸን፡ይናገራልሉ።ዶሮን፡ሲያታልሏት፡በመጫኛ፡ጣሏት፡የሚባለው፡የአባቶች፡ንግግር፡ሆኖ፡ታዬን።ኢትዮጵያ፡ለተባበሩት፡መንግሥታት፡ድርጅት፡አቅርባ፡የነበረችው፡ጥያቄ፡-ኤርትራ፡ከእናት፡አገሯ፡ያላንዳች፡ማመንታት፡እንድትቀላቀል፡ነበረ።በቀረበው፡ጥያቄ፡ላይ፡ክርክር፡ታደርግ፡በነበረችበት፡ወቅት፡ያልነበሩ፡እና፡ታሪከን፡የማያውቁ፡የዘመኑ፡ወጣቶች፡በዚያን፡ታሪካዊ፡ግዜ፡ለሥልጣን፡ጉጉት፡ያልነበራቸው፡ግን፡የሀገር፡ፍቅር፡ነበራቸው።አባቶች፤እናቶች፤ወንድሞቻችንና፡እህቶቻችን፡ኤርትራ፡ከእናት፡ኢትዮጵያ፡ጋር፡መዋሃድ፡አልለብባት፡የሚሉት፡ወገኖች፡መጠናከር፡ይታትይ፡ነበረ።አንዳንድ፡ከተደለሉ፡ወገኞች፡አቋማቸውን፡በመለዬት፡ያስሰሙት፡የነበረው፡እሮሮና፡አቤቱታ፡በአያሌው፡ድምፃቸው፡እዬጐልላ፡ተሰማ።ከዚያም፤የተባበሩት፡መንግሥታት፡ዋና፡ጸሐፊ፡አንዚ፡ማቲንዞ፡የተባሉትን፡የላቲን፡አመሪካ፡ተወላጅ፤የሕዝቡን፡አቋም፡ባሕልና፡ስሜቱን፡ሁኔታ፡በቅርብ፡ሆነው፡አጥንተው፡መግለጫ፡እንዲያቀርቡ፡ሾሟቸው።አንዚ፡ማቲንዞም፡አሥመራ፡ላይ፡ከአንድ፡ዓመት፡በላይ፡ከቆዬ፡በኋላ፤ያቀረቡትን፡መግለጫ፡በተባበሩት፡መንግሥታት፡ጉባዔ፡ላይ፡ተሰማ።ኢጣልያ፡በበኩሏ፡ችግር፡ለመፍጠር፡ወዲያና፡ወዲህ፡በማለት፡የምታደርገው፡ልዩ፡ልዩ፡የሥነ፡መንግሥት፡ስብከት፡(ፖለቲካ፡ፕሮፓጋንዳ)፡በላቲን፡አመሪካ፡አገሮች፡ድጋፍም፡ነበራት።እናም፤የዋና፡ጸሀፊ፡መልክተኛ፡ከላቲን፡አመሪካ፡ስለ፡ነበረ፡የሥራ፡ግዜያቸውን፡አጠናቅቀው፡ሲመልለሱ፡ባቀረቡት፡መግለጫ፡ሙሉ፡በሙሉ፡ከኢትዮጵያ፡ጋር፡እንድትቀላቀል፡ባለ፡መሆኑ፤በኅብረት፤ሱታፌ፡(ፌዴሬሽን)፡እንድትዋሃድ፡የተደረገው፡መልእክተኛው፡ባቀረቡት፡አስተያየት፡ምክንያት፡ነበረ።ሆኖም፤በተባበሩት፡መንግሥታት፡ጉባዔ፡ይደረግ፡የነበረው፡ክርክር፡ልዩ፡ልዩ፡መልክ፡የያዘ፡ነበረ።ግብፅ፤ፓኪስታንና፡ሌሎችም፡የዓረብ፡አገሮች፡አስቸግረው፡ነበረ።ይኸውም፡ኤርትራ፡ነፃ፡ትውጣ፡የሚሉም፡የኢጣልያንን፡ሐሣብ፡የሚደግፉ፡ወገኖችም፡ነበሩ።

ይህን፡ሐሣብ፡ከሚቃወሙት፡መንግሥታት፡አንዷ፡ሩሲያ፡ኢትዮጵያ፡በጠላት፡የተወረረችው፡የባሕር፡
በርር፡ስላልነበራት፡ነበረ።ስለዚህ፣የአሰብ፡ባሕር፡በርር፡የግዛቷ፡ክፍል፡ስለ፡ነበረ፡እንዲመልለስልላት፡
ብላ፡ሐሣብ፡አቀረበች።በዚያን፡ወቅት፡ሱዳን፡የቅኝ፡ግዛቷ፡ስለ፡ነበረች፣እንግሊዝም፡በበኩሏ፡የኤርት
ራ፡የምዕራቡ፡ክፍል፡ከሱዳን፡ጋር፡እንዲቀላቀል፡በማለት፡ሐሣብ፡አቀረበች።ክርክሩ፡ቀጥሎ፡ብዙ፡ግዜ፡
የሐሣብ፡ልውውጥ፡ተደርረገ።በኋላም፡ጠንካራና፡ወሳኙ፡የነበረው፡የአመሪካ፡መንግሥት፡ዋና፡ጸሐፊ፡
(ሴክሬታሪ፡አፍ፡ስቴት)፡የነበሩት፡ፎስተር፡ደለስ፣ኤርትራ፡በሱታፌ፣ኀብረት፡(ፌዴሬሽን)፡ከኢትዮጵ
ያ፡ጋር፡እንድትዋሃድ፡የሚለውን፡ሐሣብ፡ስለ፡ደገፉ፡ይኸው፡ሐሣብ፡በድምፅ፡ብልጫ፡አልፎ፡በተባበሩ
ት፡መንግሥታት፡ድርጅት፡ጠቅላላ፡ጉባዔ፡ፀድደቀ።ኢትዮጵያም፡ሌላ፡አምማራጭ፡ስላልነበራት፡ተቀ
ብበለች”።

ስለዚህ፡ኸርማን፡ኮኸን፡እያወቁ፡እንዳላወቁ፡ሆነው፡በአሁኑ፡ግዜ፡ሕዝቡ፡አልፈልገም፡ነበረ፡
ብለው፡የተናገሩት፡ቃል፡ከዕውነት፡የራቀ፡ነው።ፍላጐታቸውን፡ዳር፡ለማድረስ፡ወያኔን፡አዲስ፡አበባ፡
አምጥተው፡ባስቀምመጡበት፡ወቅት፣ይህን፡አድርግ፡ወይም፡አታድርግ፡ብለው፡ያልሰጡትን፡መመሪ
ያ፡ዛሬ፡ቢያወሩት፡ከ፹፭፡(85)፡ሚሊዮን፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡የአንድ፡ነጠላ፡ሰው፡አገልግሎት፡ለአመ
ሪካ፡ይጠቅማል፡ብለው፡የመርረጡት፡ሐሣብ፤ያሳዘኑትን፡ጨዋ፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ጋር፡አገራቸውን፡
የሚያስታርቁብበት፡ዘዴ፡ሊሆን፡አይችልም።የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ምሬት፡በኸርማን፡ኮኸን፡ብቻ፡ሳይሆ
ን፡በቀድሞው፡የአመሪካ፡ርዕሰ፡ብሔር፡(ፕሬዚደንት)፡ካርተር፡ጭምምር፡ነው።ባደርረጉት፡ማብበረታ
ታት፡የመርረጡት፡ሰው፡የሚያደርገው፡የግፍ፡ሥራ፡የሚርረሣ፡ስላልሆነ፡የኢትዮጵያም፡ሕዝብ፡ከኸር
ማን፡ኮኸንና፡ከርሳቸው፡ጋር፡የተባበሩትን፡ወገኖች፡ሆልሉ፡ላይ፡እንዳዘነ፡ማወቅ፡ይግገብባቸዋል።ዛሬ፡
ኢትዮጵያንና፡ሕዝቧን፡በመከራ፡ማጥ፡እያንገላታ፣በረሃብ፡እዬቀጣ፡ፈላጭ፡ቆራጩ፡የወያኔ፡አስተዳደ
ር፡መሆኑ፡ሥውር፡አይደለም።የአገሩን፡ተወልላጅ፡ገበሬ፡እያብባረረ፤ለም፡መሬቱን፡እዬነጠቀ፡ለባዕድ፡
ከበርቴዎች፡ይሸጣል።ለትውልድ፡የሚተላለፍ፡ችግር፡እያዝዘጋጀ፡የውሸት፡ሕዝባዊ፡አገዛዝ፡(ዴሞክራ
ሲ)፡ለሚያካሄደው፡ቀጣፊ፡ለገሠ፡ዜናዊ፡አምመራር፡የአመሪካ፡ስለላ፡መዋቅር፡(ሲአይኤ)፡ተወካዮች፡
በአዲስ፡አበባ፡ሁኔታውንና፡የሚያደርገውን፡ማሠር፣መግደል፣አገር፡ማጥፋቱን፡በደል፡ዐውቀው፡መግለ
ጫ፡(ሪፖርት)፡አላደረጉም፡ቢባል፡ሥራቸውን፡ረስተውታል፡ማለት፡ይቻላል።ኸርማን፡ኮኸን፡ስለ፡ኤ
ርትራ፡መገንጠል፡እንደ፡እማያውቁ፡ሆነው፡ዛሬ፡የሚተርርኩት፡የመንግሥታዊ፡ዘዴ፡(ዲፕሎማሲ)፡ሥ
ውር፡አስተሣሠባቸውን፡ኢትዮጵያውያን፡አያውቁም፡የሚሉ፡ከሆነ፡ተሣሥተዋል።ማን፡ከካውና፡ማን፡
አበሰለው።እርሳቸውና፡እርሳቸውን፡የመሰሉት፡የኢትዮጵያን፡አንደነት፡የማይፈልልጉ፡ወገኖች፡መኖራ
ቸውን፡ሁልሉም፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ያውቀዋል።ይልቁንስ፡ለወያኔ፡ያስረከቧት፡ኢትዮጵያን፡ካለችበ
ት፡ችግር፡የምትላቀቅበትን፡በሚያውቁት፡መንግሥታዊ፡ዘዴያቸው(ዲፕሎማሲያቸው)ና፡ምክራቸው
ን፡ለሚመለከተው፡ክፍል፡ቢያሳውቁና፡ያደረጉትን፡ስሕተት፡እንዲታርረም፡ቢጥሩበት፡የተሻለ፡ይሆና
ል።ይህን፡ቢፈጽሙ፡ያሳዘኑትና፡ያስቀዬሙት፡የኢትዮጵያ፡ሕዝብ፡ይቅርታ፡ያደርግላቸዋል።ሳያደርጉ
ት፡ቢቀር፡ግን፡ፍርዱን፡ከሚያምነው፡አምላክ፡ዘንድ፡ያገኙዋል።

## ኢትዮጵያ፡በእግዚአብሔር፡እርዳታና፡በልጆቿ፡ትግል፡አትጠፋም።በነፃነቷ፡ለዘላለም፡ትኖራለች።

ከዜናማርቆስ፡መርሐ፣ካናዳ።
እ፡ጦማር፡- zienamarqos@yahoo.com